የአፋር ብሔራዊ □ልላዊ መንግስት

የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም

መወሰኛ አዋጅ

ሀምሌ 2001 ዓ.ም

ሰመራ፤

አዋጅ ቁጥር 49/2001 ፕ.ም.

የአፋር ብሔራዊ □ልላዊ መንግስት

የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መወሰኛ አዋጅ

መፅቢጸ

የመሬት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ መሆኑ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ቴሞ□ራሲጸዊ ሪዩ ብሊ□ ሕቱመንግሥት በመረጋገጡ፣

በ1994 ፕ.ም በተሻሻለ□ □አፋር ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 38 ንዑስ አንቀፅ 3 የመሬት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ መሆኑ በመደንገጉ፣

መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን ለማስተዳዳር ለክልሎች የተሰጠው ሥልጣን በሥራ ላይ የሚውለው የፌዴራል መንግሥቱ በሚያወጣው ሕግ መሠረት መሆኑን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕቱ መንግሥት አንቀጽ 52/2 (መ) ስለሚደነግግና ይህንኑ ህገ-መንግስታዊ መብት መጠቀም አስፈላጊ በመሆኑ፣

በ2000 ዓ.ም የጸደቀውን የክልሉን የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ፖ'ሊሲ ለመተግበር እንዲቻል ህግ ማውጣቱ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በክልሉ ተጨባጭ ሁኔታ ላይ ተመስርቶ ዘላቂ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ በማውጣትና በመተግበር የተፈጥሮ ሀብቶችን በዘላቂነት በመጠበቅና በማልማት ለመጪው ትውልድ ማስተላለፍ በማስ□ለቱ፣

በ□ልሉ □ሚኖሩ የተለያዮ የገጠር መሬት የጁዞታ ዓይነቶችን ማለትም በግለሰብ፣ በወል እና በመንግሥት ሥር የሚገኙ ጁዞታዎችን በስፋት፣ በአቅጣጫና በመሬት የመጠቀም መብቶች ለመለየት የሚያስችል የመረጃ ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

አርብቶ አደሮችን፤ ከፊል አርብቶ አደሮችንና የግብርና ኢንቨስተሮችን ከማበረታታት አኳያ የሚታዩ ችግሮችን በመቅረፍ ምቹ የሆነ የገጠር መሬት አስተዳደር ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

በገጠር መሬት የመጠቀም መብት መረጋገጥ በክልሉ ለሚሰማሩ የግል ባለሃብቶች ዋስትና የሚሰጥና ወደ ክልሉ እንዲመጡ የሚጋብዝ እንደሆነ ስለሚታመን፤

ቀደም ሲል የክልሉ ማህበረሰብ ሲገለገልበት የነበረው ልማዳዊው የገጠር መሬት አጠቃቀምና አስተዳደር ስርዓት መላላት ለተፈጥሮ ሃብት ውድመትና ለእርስ በርስ ግጭቶች መንስዔ እየሆነ በመምጣቱ፤

የሴቶች የመሬት ይዞታ ባለቤትነትና የመጠቀም መብት ያለምንም ተጽእኖ መረጋገጥ ለምርትና ምርታማነት እንዲሁም የአካባቢ ልማትን ለማፋጠንና ለማረጋገጥ አስፈላጊነቱ በመታመኑ፣

ጥምር የሰብልና የእንስሳት ምርት እንቅስቃሴ በሰፈነባቸው አካባቢዎች የአፈር መሸረሸርና የደን መመናመን አደጋ በመኖሩ አርብቶ አደሩና ከፊል አርብቶ አደሩ አስፈላጊውን እንክብካቤ እንዲያደርግ፤ በጃዞታው የመጠቀም መብቱ እንዲጐለብትና እንዲጠናከር ምቹ የሕግ ማዕቀፍ መአ□ሩ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የግብርና ምርት ግብይቱ በሰፊ መሰረት ላይ ተመስርቶ ቀጣይና አስተማማኝ እንዲሆን የግብርናውን ምርት ማሳደግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በክልሉ በአብዛኛው በጐሣ ላይ በተመሠረተው የወል የመሬት ይዞታ ስሪት ውስጥ ለተፈጥሮ ሀብት አያያዝና አጠቃቀም እንዲሁም የግል ባለሃብቶችን ከማበረታታት አኳያ ተስማሚ የገጠር መሬት አስተዳደር ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፣

የፌዴራል መንግሥት ለክልሎች የክልላቸውን ተጨባጭ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ሕግ የማውጣት ሥልጣን በገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 456/1997 በአንቀጽ 17/1 የተሰጠ ስለሆነ በተሻሻለው የአፋር ክልል ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀፅ 3 /ሀ/ መሠረት የሚከተለው ታ□ጿል፡፡

ክፍል አንድ

□ቅላላ

አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የአፋር ብሔራዊ □ልላዊ መንግስት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም አዋጅ ቁጥር 49/2001 ዓ.ም ተብሎ ሊ□ቀስ ይችላል።

አንቀጽ 2. ትርጉሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

1. «ክልል» ማለት የአፋር ብሔራዊ □ልላዊ መንግስት ማለት ነው።
2. «የገጠር መሬት» ማለት ከማዘጋጃ ቤት ክልል ውጭ ወይም አግባብ ባለው ሕግ «ከተማ» ተብሎ ከሚሰይመው ውጪ ያለ ማንኛውም መሬት ነው።
3. «የገጠር መሬት አስተዳደር» ማለት በገጠር መሬት ይዞታ ላይ ዋስትና የሚሰጥበት፣ የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ የሚተገበርበት፣ በገጠር መሬት ተጠቃሚዎች መካከል የሚነሱ ግጭቶች የሚፈቱበትና ማንኛ □ም □ሀገር መሬት ተጠቃሚ መብትና ግዴታዎች የሚተገበሩበት እንዲሁም የባለይዞታዎችን ማሳዎችና የግጦሽ መሬትን መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን ለተጠቃሚዎች እንዲደርሱ የሚደረግበት ሂደት ነው።
4. «የገጠር መሬት አጠቀቃም» ማለት የገጠር መሬትን በእንክብካቤ ይዞ ዘላቂነት ባለው መንገድ ለተሻለ ጠቀሜታ እንዲውል የሚደረግበት ሂደት ነው።
5. «የገጠር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ» ማለት አካላዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ የገጠር መሬት ሊሰጥ ከሚችለው የተለያዩ የመሬት አጠቃቀም አማራጮች መካከል የሚወሰኑበትና ተግባራዊ የሚደረጉበት የአሠራር ዘዴ ነው።
6. «□ጅዞታ መብት» ማለት ማንኛውም አርብቶአደርና ከፊል አርብቶአደር የገጠርን መሬት በእንስሳት እርባታ፤ በእርሻ ስራና በተፈጥሮ ሃብት ልማት ተግባር ላይ ለማዋል፣ ለማከራየትና ለቤተሰቡ አባልና ለሌሎች በህግ መብት ለተሰጣቸው ወራሾች ለማውረስ የሚኖረው መብት ሲሆን፣

በመሬቱ ላይ በጉልበቱ ወይም በገንዘቡ ንብረት ማፍራትና ይህንንም በመሬቱ ላይ ያፈራውን ንብረት መሸጥ፣ መለወጥና ማውረስንም ጁፊ ምራል።

7. «የቤተሰብ አባል» ማለት የይዞታ ባለመብቱን መተዳደሪያ ገቢ በመጋራት በቋሚነት አብሮ የሚኖር ማንኛውም ሰው ነው።
8. « ሞግዚት» ማለት ለአካለ መጠን ያልደረሱና ወላጆቻቸውን በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ያጡ ልጆችን የሚያሳድግ ሕጋዊ ሰው ነው።
9. « ልጅ» ማለት በስጋ የተወለደ ወይም የጉዲፈቻ ልጅ ነው።
10. « የመጠቀም መብት» ማለት በዚህ አዋጅ መሰረት በገጠር መሬት የመገልገልና የሚገኘውን ምርት የመጠቀም መብት ነው።
11. « የመሬት ተጠቃሚ» ማለት በገጠር መሬት የመገልገልና የሚገኘውን ምርት የመጠቀም መብት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ነው።
12. « አርብቶአደር» ማለት የግጦሽ መሬትን በመያዝና ከቦ□ □□ ቦ□ በመንቀሳቀስ በዋነኛነት እንስሳት በማርባት ኑሮውን ከእንስሳት ሀብት በሚጸቀኘው ምርት ላይ የመሠረተ የገጠሩ የሕብረተሰብ ክፍል አባል ነው።
13. « ከፊል አርብቶአደር» ማለት በዋነኛነት እንስሳት በማርባትና በተወሰነ ደረጃ ከእርሻ በሚገኝ ምርት ላይ ኑሮውን የመሠረተ የገጠር ህብረተሰብ ክፍል ነው።
14. «አነስተኛ □ጁዞታ መጠን» ማለት ምርታማነቱ የአንድን አርብቶአደር እና ከፊል አርብቶአደር ቤተሰብ የምግብ ዋስትና ሊያረጋግጥ የሚችል የገጠር መሬት ይዞ□ (ለፅፈሽ፣ ለፐመ□ዊ ሰብል፣ ለቋሚ ሰብል፣ ለመኖሪያ ቤትና ለጓሮ አትክልት የሚበቃ) መጠን ነው።
15. « □ፅል ጁዞ□» ማለት በአርብቶ አደሮች እና በከፊል አርብቶአደሮች ወይንም በሌሎች በህግ መብት በተሰጣቸው አካላት በፅል ጁዞ□ ሥር ያለ የገጠር መሬት ነው።
16. « □ጋራ ጁዞ□» ማለት ቁጥራቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ሰዎች በአንድ መሬት ላይ ያልተከፋፈለ የይዞታ ባለመብቶች ሆነው መሬቱን ሳይከፋፈሉ ከዚሁ ከመሬቱ የሚገኘውን ጥቅም እየተጋሩ የሚጠቀሙበት መሬት ነው።

17. « □ወል ጁዞ□» ማለት ከመንግሥት ወይንም ከግል ይዞታነት ውጪ የሚገኝ እና የአካባቢው ነዋሪዎች በጋራ ይዞታነት የሚጠቀሙበት ሲሆን ለግጦሽ፤ ለደንና ለሌሎች ማህበራዊ አገልግሎቶች እየዋለ ያለ □ዙ□ር መሬት ነው::
18. « የመንግስት ይዞ□ » ማለት በፌዴራል ወይንም በክልል መንግሥት ተከልሎ የተያዘና ወደፊትም የሚከለል የገጠር መሬትን የሚገልጽ ሲሆን፣ የደን መሬቶችን፣ የዱር እንስሳት ጥበቃ ቦታዎች የመንግሥት እርሻዎችን፣ የማዕድን መሬቶችን ሃይቆችን፣ ወንዞችንና ሌሎችን በተመሳሳይ መልኩ የተያዙትን ያጠቃልላል::
19. « □ጁዞ□ ማረ□ቱ□ □ብተር» ማለት በገጠር መሬት የመጠቀምን መብት ለማረጋገጥ አግባብ ባለው አካል የሚሰጥ ሰነድ ነው::
20. «የመሬት ምዝገባ» ማለት በገጠር መሬት የመጠቀም መብትና ባለይዞታነት □ሚቸለጽበት መረጃ የማሰባሰብና የማጠናቀር ሂደት ነው::
21. « የመሬት መረጃ ሥርዓት» ማለት የመሬት መረጃዎችን በማሰባሰብ በመተንተንና በአግባቡ እንዲያዙ በማድረግ ለተለያዩ ተጠቃሚ ክፍሎች የማሰራጨት ሥርዓት ነው::
22. « አግባብ ያለው አካል» ማለት የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓት መስፈኑን ለመከ□ተል በህፅ □ሚቋቋመው አካል ነው::
23. « ሽፅሽፅ »/Redistribution/ ማለት በመስኖ መሬት ወይም አስፈላጊነቱ በሕግ በሚወሰን መሬት ላይ ብቻ □ሚፈጸም የማሽጋሸግ ተግባር ነው::
24. « ክፍፍል » / Distribution/ማለት ያልተያዘ ወይም የተለቀቀ የገጠር መሬት መሬት ለሌላቸው ወይም መሬት ላነሳቸው ሰዎች ማከፋፈል ማለት ነው::
25. « ኪራይ» ማለት ባለሃብትም ሆነ ሌላ ሕጋዊ አካል ከአርብቶ አደሮች ወይም ከከፊል አርብቶ አደሮች ለተወሰነ ጊዜ መሬትን የሚከራዩበት ሥርዓት ነው::
26. « የሊዝ ኪራይ» ማለት ባለሃብቶች ከመንግሥት ለተወሰነ ጊዜ መሬትን የሚከራዩበት ሥርዓት ነው::
27. «□ሕ□ብ ዓቅም» ማለት በመሠረተ ልማት አውታሮች ማለትም በትምህርት፣ በጤና፣ በመንገድ፣ በውሃ ወዘተ. ተቋማት የሚገኝ የሕዝብ የጋራ አገልግሎት ማለት ነው::

28. «ሰ□» ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ማለት ነው።

29. «□ተረጋጋ ኑሮ» ማለት በመንግስት ወይም መንግስታዊ ባልሆነ ድርጅቶች የሚሰሩ መሰረተ ልማቶችን በመከተል አርብቶ አደሩ ቋሚ ኑሮ ለመመስረት በፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የሚደረግ የመስፈር ተግባር ነው።

አንቀጽ 3. □□ታ አገላለጽ

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው በሙሉ የሴትንም ጾታ ያካትታል።

አንቀጽ 4. የአዋጁ ተፈጻሚነት ወሰን

1. ይህ አዋጅ በአፋር ብሔራዊ □ልላዊ መንግሥት ውስጥ በሚገኝ ማንኛ□ም የገጠር መሬት ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ለደን፤ ለዱር እንስሳት ጥበቃ፤ ለብዝሃ-ሕይወት ሀብትነት፤ ለተፈጥሮ ሃብትና ለአካባቢ ጥበቃ፤ ለማዕድን ልማትና ለመሳሰሉት የተከለሉ መሬቶችን መንከባከብና ማልማትን በተመለከተ የወጡ ልዩ ህጎች እንደተደነገጉባቸው መስኮች ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

ክፍል ሁለት

የአርብቶ አደሮችን በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ስለማረጋገጥ

አንቀጽ 5. □ግጦሽ መሬት ስለማግኘትና ስለመጠቀም

1. የክልሉ አርብቶ አደሮች በግጦሽ መሬታቸው ያለ ጊዜ ገደብ የመጠቀም መብት አላቸው።
2. አርብቶ አደር ሴቶች ከወንዱ እኩል በግጦሽ መሬት የመጠቀም መብት አላቸው።
3. አርብቶ አደሩ እየተጠቀመበት የሚገኘው የተፈጥሮ ግጦሽ መሬትና የመንቀሳቀሻ ቦታ ተለይቶ ይከለላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

4. አርብቶ አደሩ በወል በሚጠቀምበት የተፈጥሮ ግጦሽ መሬት ውስጥ በግል ይዞታነት የሚገኙ ይዞታዎችን ባለይዞታው በውርስ ለልጆቻቸው ወይም ለሌሎች ህጋዊ ወራሾች ሊያስተላልፉ ይችላሉ።
5. 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ አርብቶ አደር በቋሚ እርሻ ስራ ለመሰማራት ከፈለገ በክልሉ አግባብ ያለው አካል በመጠየቅ በነጻ መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት አላቸው።
6. የክልሉ መንግስት በሚያዘጋጀው የተረጋጋ ኑሮ ለመምራት የሚያስችል ፕሮግራም ተጠቃሚ መሆን የሚፈልጉ አርብቶ አደሮች በፈቃደኝነት የመስፈር መብታቸው የተረጋገጠ ነው።
7. በአርብቶ አደሩ ውስጥ የሚገኙ አረጋውያን፣ አቅመ ደካማና አካል ጉዳተኞች የወል መሬትን የመጠቀም መብት የተመለከቱ ባህላዊ ልምዶች እንደተጠበቁ ሆነው መንግስት አስፈላጊውን የማጠናከሪያ ድጋፍ ይሰጣል። □ር□ሩ በደንብ ይወሰናል።
8. የአርብቶ አደሩን የወል መጠቀሚያ መሬት ወደ ግል ይዞታነት ማዞር የተከለከለ ነው።
9. አርብቶ አደሩ በወል ይዞታነት(ለግጦሽ እና ለማህበራዊ አገልግሎት) እየተጠቀመበት ያለው መሬት ለግል ባለሃብቶች አይሰጥም። ሆኖም ግን መንግሥት በመሬት ባለቤትነቱ የወል ወይም የጋራ የገጠር መሬት ጁዞታዎችን እንደአስፈላጊነቱ በአርብቶ አደሩ ፍላጎትና ውሳኔ □□ ፅል ጁዞታነት እንዲቀየሩ ሊያደርግ ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
10. ለአርብቶ አደሮች ቅድሚያ በመስጠት፣ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ከክልሉ የልማት ዓላማዎች □ር □□ታየ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል።

አንቀጽ 6. <u>የአርብቶ አደሮችን □ወል ይዞታዎች ስለመለካት፣ ስለመመዝገብና □ጁዞታ ማረጋገጫ ደብተር ስለመስጠት</u>

1. በአርብቶ አደሩ በወል የተያዙ መሬቶች በተጠቃሚው ማህበረሰብ □ጁም በአካባቢው ተጠቃሚዎች መጠሪያ ስም እየተለካ ይመዘገባል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

2. □ጅዞ□ ማረጋገጫ □ብተር በተጠቃሚ□ ማህበረሰብ ወይም በአካባቢ ተ□ቃሚ ተወካይ እጅ ይሰጣል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

አንቀጽ 7. <u>የክርክሮች አወሳሰን</u>

1. በአርብቶ አደሮች መካከል የሚነሱ የይዞታ ክርክሮች ቀደም ሲል ይሰራበት በነበረው ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ይፈታሉ፡፡
2. ይህንን ባህላዊ የግጭት አፈታት ስርዓት ለማጠናከርና የማስፈጸም አቅምን ለማሳደግ የክልሉ መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በሽማግሌዎች እርቅና ድርድር ያልተስማማ ወገን ለወረዳ መደበኛ ፍ/ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተሰጠው ውሣኔ ያልተስማማ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 በተሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡ በዚህ ደረጃ በአ/ቤት የሚሰጥ ውሣኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡
6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት በተሰጠ ውሣኔ መሠረታዊ የሕግ ስህተት ይኖራለ ተብሎ ከታሰበ በሰበር ችሎታ ሊታይ ይችላል፡፡

አንቀጽ 8. <u>□ተፈጥሮ ሃብትን ስለመጠበቅና ስለመንከባከብ</u>

1. በአርብቶ አደሩ ሲሰራበት የቆየው ባህላዊ የተፈጥሮ ሃብት ጥበቃና አጠቃቀም ስርዓት እንዲጎለብት መንግስት አስፈላጊውን ድጋፍ ይሰጣል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

□ኣል ሶስት

የከፊል አርብቶ አደሮችን በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ስለማረ□ቱ

አንቀጽ 9. የገጠር መሬት ስለማግኘትና ስለመጠቀም

1. ከፊል አርብቶ አደሩ በወል የሚጠቀሙበት የግጦሽ መሬት ይዞታቸው የተጠበቀ ነው፡፡
2. ከፊል አርብቶ አደሮች በወል ለግጦሽ በያዙት መሬት ላይ ለአርብቶ አደሮች የተሰጠው መብትና ግዴታ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
3. ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነና በእንስሳት እርባታ፤ በእርሻ ሥራና በተፈጥሮ ሃብት ልማት ሊተዳደር የሚፈልግ ማንኛ□ም □□ልሉ ከፊል አርብቶአደር የገጠር መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት አለው፡፡
4. የከፊል አርብቶ አደሮች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የጊዜ ገደብ □ለ□ም፡፡
5. በእንስሳት እርባታ፤ በእርሻ ሥራና በተፈጥሮ ሃብት ልማት መሰማራት □ሚ□ልቱ የክልሉ ሴቶች መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት አላቸው፡፡
6. በእንስሳት እርባታ፤ በእርሻ ሥራና በተፈጥሮ ሃብት ልማት መሰማራት የሚፈልጉ የገጠር ወጣቶች በየአካባቢው ካለው የወል ወይም የመንግሥት መሬት የማግኘትና የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል፡፡ □ር□ሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
7. ባልና ሚስት በይዞታቸው እኩል የመጠቀም መብት አላቸው፡፡ ከጋብቻ በፊት የነበራቸውን ይዞታ በጋብቻ ምክንያት አያጡም፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
8. □ማ□ራዎች □ጁም □ኬተሰብ ኃላፊ ሴቶች በይዞታቸው የመጠቀም ሙሉ መብት አላቸው፡፡
9. ባሎቻቸው በመንግሥታዊ አገልግሎት ወይም በሌላ ሥራ ላይ የተሰማሩ የገጠር ሴቶች በይዞታቸው የመጠቀም መብት አላቸው፡፡
10. ወላጆቻቸውን በሞት ወይም በሌላ ምክንያት ያጡ ልጆች ዕድሜአቸው 18 ዓመት እኪሞላቸው ድረስ ይዞታቸውን በሞግዚታቸው አማካኝነት የመጠቀም መብት አላቸው፡፡

11. ጽዞታ ያላቸው ባል ወይም ሚስት በሌላ አካባቢ መኖር ወይም በሞት መለየት የቤተሰቡን ይዞታ የመጠቀም መብት አያሳጣም።
12. ከፊል አርብቶ አደሮች ለጋራ ጠቀሜታ የሚሆን ማለትም ለማህበራዊ፣ ለባሕላዊና ለእምነት ጉዳዮች የሚሆን መሬት በነጻ የማግኘትና የመጠቀም መብት አላቸው።
13. ማንኛውም ከፊል አርብቶ አደር ቤተሰብ አባል፣ ከቤተሰቡ በስጦ□ □ጽም በውርስ ወይም አግባብ ካለው አካል የገጠር መሬት ሊያገኝ ይችላል።
14. ማንኛ□ም በእንስሳት እርባታ፤ በእርሻ ሥራና በተፈጥሮ ሃብት ልማት ለመተዳ□ር □ሚ□ልፅ □□ልሉ ከፊል አርብቶ አደር በፈቃደኝነት ላይ በተመሰረተ የተረጋጋ ኑሮ ለመምራት በሚያስችል ፕሮግራም መሬት □ማፅኘትና የመጠቀም መብት አለው።
15. አረጋውያን፣ አቅመ ደካማና አካል ጉዳተኛ ቤተሰቦች □ጽዞታ ባለቤት የመሆንና የመጠቀም መብት አላቸው።
16. መንግሥት በመሬት ባለቤትነቱ የወል ወይም የጋራ የገጠር መሬት ጽዞታዎችን እንደአስፈላጊነቱ በከፊል አርብቶ አደሩ ፍላጎትና ውሳኔ □□ ፅል ጽዞታነት እንዲቀየሩ ሊያደርግ ይችላል።
17. ከፊል አርብቶ አደሩ ለሕ□ብ ዓ ቅም ሲባል ጽዞታውን እንዲለቅ ሲደረግ በመሬቱ ላይ ላደረገው ማሻሻያና ላፈራው ንብረት ተመጣጣኝ ካሣ በቅድሚያ ይከፈለዋል። በለቀቀው መሬት ምትክ ተመጣጣኝ ተለ□□ መሬት እንዲያገኝ ይደረጋል። ባለይዞታው መሬቱን እንዲለቅ □ሚ□ረቱ□፣

ሀ. በፌዴራል መንግሥት ከሆነ የሚከፈለው ካሣ ተመን በፌዴራል ሕግ ይወሰናል።

ለ. በክልል መንግሥት ከሆነ የካሣ ተመኑ የክልሉ መንግሥት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ እና ለ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ የከፊል አርብቶ አደሩ የህልውናው መሰረት የተፈጥሮ ግጦሽ ስለሆነ ከግጦሽ መሬቱ በሚፈናቀልበት ወቅት ከመሬቱ የሚያገኘው ጥቅም ተሰልቶ ተመጣጣኝ የካሳ ክፍያ እንዲፈጸምለት ይደረጋል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

18. ማንኛ□ም የክልሉ ከፊል አርብቶ አደር በስጦታ፤ በውርስና በሌሎች ህጋዊ አግባብ ባላቸው ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር ከአንድ ጊዜ በላይ መሬት በክፍፍል ማግኘት አይችልም።

አንቀጽ 10. □ከፊል አርብቶ አደሮችን የእርሻ መሬት ስለመለካት፣ ስለመመዝገብና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ስለመስጠት

1. በከፊል አርብቶአደሮች በፅልና በ□ል ጽዞታ ሥር ያሉ የገጠር መሬቶች እንደሁኔታው ባህላዊና ዘመናዊ የቅየሣ መሣሪዎችን በመጠቀም በመቀየስ፤ የመሬት ስፋታቸውን በመለካት እንዲሁም የመሬት አጠቃቀማቸውንና የለምነት ደረጃቸውን በመለየት በ□□ረጸ□ በሚቋቋሙ የመረጃ ማዕከላት ጁመ□ክላሉ።
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 የተ□ረ□ሩት ይዞታዎች አግባብ ባለው አካል ተለ□ተ□ □ጽዞታ ድንበራቸውን የሚያሣይ ካርታ ይዘጋጅላቸዋል።
3. ማንኛ□ም ባለጽዞታ አግባብ ባለው አካል የሚዘጋጅና የመሬቱን ይዞታ ስፋት፣ አጠቃቀምና ሽፋን፣ የለምነት ደረጃና አዋሣኞቹን እንዲሁም ኃላፊነትና ግዴታን □ጸ□ □ጽዞታ ማረጋገጫ ደብተር እንዲኖረው ይደረጋል።
4. መሬቱ የባልና የሚስት የጋራ ከሆነ የይዞ□ ማረ□ቹ□ □ብተሩ በሁሉም □□ራ ባለጽዞታዎች ስም ይዘጋጃል፣ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
5. ለእማወራ ሴቶች (የቤተሰብ ኃላፊ ሴቶች) የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስማቸው ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል።
6. ባሎቻቸው በመንግሥታዊ አገልግሎት ወይም በሌላ ሥራ ተሰማርተው □ሚቶኙ ሴቶች የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር በስማቸው ተዘጋጅቶ ይሰጣቸዋል።
7. ወላጆቻቸው በሞት የተለዩአቸው ለአቅመ አዳም /ሔዋን/ ያልደረሱ ልጆች የመሬት ይዞታቸውን በሞግዚታቸው አማካኝነት ሊለካ ሊመዘገብና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር ሊሰጣቸው ይችላል።
8. □ጽዞታ መብት ለውጥ በሚደረግበት ጊዜ የይዞ□ ማረ□ቹ□ □ብተር ለ□ዓ ም ጽ□ረ□ል።
9. ከፊል አርብቶ አደሩ በወል ለሚጠቀምበት የግጦሽ መሬት □ጽዞ□ ማረጋገጫ □ብተር በተ□ቃሚ□ ማህበረሰብ ተወካይ እጅ ይሰጣል።

አንቀጽ 11. በገጠር መሬት የመጠቀም መብትን በኪራይ ስለማስተላለፍ

1. □ጅዞ□ ማረ□ቱ□ □ብተር የተሰጣቸው ከፈል አርብቶ አደሮች አስገዳጅ የሆኑ ሁኔታዎች ከተፈጠሩባቸው እነሱን በማያፈናቅል መልኩ ለሌሎች ከፈል አርብቶ አደሮች ወይንም ባለሀብቶች እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ከይዞታቸው ከግማሽ ያልበለጠውን ማከራየት ይችላሉ ። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ የኪራይ ዘመኑም፣

   ሀ. ከፈል አርብቶ አደሮች ለከፈል አርብቶ አደሮች ሲያከራዩ እስከ አምስት ዓመት ይሆናል።

   ለ. ከፈል አርብቶ አደሮች ዓመታዊ ሰብሎችን ለሚያመርቱ ባለሀብቶች የግል፤ የጋራ ወይም የወል የመሬት ይዞታቸውን ሲያከራዩ እስከ አሥር ዓመት ይሆናል።

   ሐ. ከፈል አርብቶ አደሮች ቋሚ ተክልን ለሚያመርቱ ባለሀብቶች የግል፤ የጋራ ወይም የወል የመሬት ይዞታቸውን ሲያከራዩ እስከ ሃያ ዓመት ይሆናል።

   መ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀ□ 1 ከላይ ከሀ--ሐ የተጠቀሱት እንዳሉ ሆነው አፈጻጸማቸው በደንብ ይወሰናል።

   ሠ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከሀ--ሐ የተጠቀሱት መሬቶች የኪራይ ዘመኑ ሲያበቃ በፍትሐብሔር ሕግ መሠረት ለባለይዞ□□ ጅመለሳሉ።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ (1) መሠረት የሚደረግ የገጠር መሬት ኪራይ ውል በመሬቱ የመጠቀም መብት ያላቸው የቤተሰብ አባላት ወይም በመሬቱ የመጠቀም መብት ያላቸው አባላት የጋራ ይሁን□ ማፅኘትና አግባብ ባለው አካል ጸድቆ መመዝገብ ያለበት ሲሆን፡

ሀ. እስከ ሁለት ዓመት የሚቆዩ የኪራይ ውሎች በወረዳው አስተዳደር ለምዝገባ ስልጣን በሚሰጠው አካል ጅመ□ዝላሉ፣

ለ. ከሁለት ዓመት በላይ የሚቆዩ የኪራይ ውሎች በክልል ለምዝገባ ሥልጣን በተሰጠው አካል ይመዘገባሉ፣

አንቀጽ 12. ስለገጠር መሬት ሽግሽግና ክፍፍል

1. የገጠር መሬት ሽግሽግ ማካሄድ አማራጭ የሌለው መፍትሄ ሆኖ ሲገኝ አግባብ ያለው አካል የመሬት ሽግሽጉን ከአነስተኛ የይዞታ መጠን በታች በማይሆንና የተፈጥሮ ሃብት መመናመንን በማያስከትል መልኩ ተግባራዊ ያደርጋል። □ር□ሩ በደንብ ይወሰናል።
2. ቀደም ሲል ከነበረው ይዞታ እንደየአካባቢው የሚወሰነውን ከፍተኛ □ራ መሠረት በማድረግ ከከፍተኛው ጣራ በላይ ያለ መሬት መሬት ለሌላቸውና ላነሳቸው ከፊል አርብቶአደሮች ሽፅሽፅ ጁ□ረ□ል። □ር□ሩ በደንብ ይወሰናል።
3. የገጠር መሬት ይዞታቸውን ለመስኖ አውታር ግንባታ ሲባል የሚያጡ ከፊል አርብቶአደሮች በአካባቢው ከሚዘረጋው የመስኖ ልማት ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ተ□ቃሚ እንዲሆኑ ሽግሽግ ሊደረግ ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
4. የገጠር መሬት ባለጀዞታዎች በሕይወት የሌሉና ወራሽ የሌላቸው ወይም በሰ□ራ □ጁም በአላቦታቸው አካባቢውን ለቀው የቆዩ ከሆነ ይዞታቸው መሬት አልባ ለሆኑ ወይም መሬት ላነሳቸው አርብቶ አደሮች እና ከፊል አርብቶ አደሮች በክፍፍል ሊሰጥ ይችላል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
5. በመንግሥት እና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወጪ ተሰርተው ለከፊል አርብቶአደሮች የሚሰጡ የመስኖ መሬቶች በአግባቡና በፍትሃዊነት ለመጠቀም እንዲቻል ክፍፍል ሊካሄድ ይችላል፣ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል።
6. ለእንስሳት እርባታ፤ ለእርሻ ሥራና ለተፈጥሮ ሃብት ልማት ሊውሉ የሚችሉ፣ በግል ያልተያዙ፣ የወልና የመንግሥት መሬቶች በአካባቢው ለሚገኙ መሬት አልባ ወጣቶችና መሬት ላነሳቸው ከፊል አርብቶ አደሮች ክፍፍል ሊ□ረፅ ይችላል።

አንቀጽ 13. □እርሻ መሬት አነስተኛ □ለል ስለመ□ሰንና ኩታገጠም ይዞታን ስለማበረታታት

1. ቀደም ሲል የነበረው የዝናብም ሆነ በመስኖ የሚለማ የአንድ ቤተሰብ የመሬት ጁዞታ ስፋት እንዳለ ሆኖ ወደፊት የሚሰጠው ይዞታ መጠን፣

   ሀ. በመንግሥትና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ወጪ ተሠርቶ ለአርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶአደሮች የሚሰጥ የመስኖ መሬት ከሆነ መጠኑ ከግማሽ ሄክ□ር ማነስ የለበትም።

ለ. በዝናብ የሚለማ ሲሆን አነስተኛ □ጁዞታ መጠን ከአንድ ሄ□ታር በታች መሆን የለበትም::

ሐ. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ሀ እና ለ የተጠቀሰው እንዳለ ሆኖ የአንድ ቤተሰብ ከፍተኛው በመስኖ ሆነ በዝናብ የሚለማ የመሬት ይዞታ መጠን እንደየአካባቢው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታ እንዲሁም የለምነት ደረጃ በጥናት ታይቶ ይወሰናል:: አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል::

2. የገጠር መሬት ይዞታ በውርስ በሚተላለፍበት ወቅት የሚተላለፈው ይዞ□ መጠን ከአነስተኛ□ □ጁዞታ መጠን በታች ከሆነ መሬቱን ሳይከፋፈሉ እንዲጠቀሙ ይደረጋል:: □ር□ሩ በደንብ ይወሰናል::
3. ባልና ሚስት በሚፋቱበት ወቅት ይዞታቸው ከአነስተኛ □ለል በታች ከሆነ ከማከፋፈል ውጭ በሌላ አማራጭ እንዲጠቀሙ ይደረጋል፣ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል::
4. አነስተኛ ማሳዎችን ለማሰባሰብና ለልማት አመቺ ለማትረፅ በከፊል አርብቶ አደሩ ሙሉ ፈቃደኝነት ላይ ተመስርቶ የይዞታ ልውውጥ እንዲያደርጉ ጁበረ□□ሉ:: □ር□ሩ በደንብ ይወሰናል::
5. □ጁዞ□ ል□ሁዓ ለማትረፅ □ቃ□ኛ የሆኑ ከፊል አርብቶ አደሮች ልውውጡን ሌሎች እንዲያውቁት በወረዳ ደረጃ ስልጣን በሚሰጠው አካል አማካይነት እንዲሰራጭ ይደረጋል፣ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል::
6. በከፊል አርብቶአደሩ ፍላጎትና ተሳትፎ የሚከናወን የማቋቋምና የመንደር ምሥረ□ ፕሮግራም የመሬት ኩታገጠምነትን መሠረት ያደረገ ይሆናል:: ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል::

አንቀጽ 14. <u>በገጠር መሬት የመጠቀም መብትን ስለማስተላለፍ</u>

1. ማንኛውም የመሬት ባለይዞታ በቁ□ር መሬት የመጠቀም መብቱን ይዞ ከባለ ሀብት ጋር በሚገባው ውል መሠረት የጋራ ወይም የሽርክና ሥራ ሊሠራ ይችላል:: ውሉም አግባብ ባለው አካል ፀድቆ መመዝገብ አለበት:: ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል::
2. ማንኛ□ም ባለጁዞታ በገጠር መሬት የመጠቀም መብቱን ለቤተሰቡ አባላት የማውረስ መብት አለው::

3. ማንኛ□ም በገጠር መሬት የመጠቀም ወይም የይዞታ ባለቤትነት መብት የተሰጠው ሕጋዊ አካል በመሬቱ ላይ በጉልበቱና በገንዘቡ ያፈራውን ሀብት ለሌላ ሕጋዊ አካል የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የመስጠት፣ የማውረስና በዋስትና የማስያዝ መብት አለው።

አንቀጽ 15. <u>የክርክሮች አወሳሰን</u>

1. የገጠር መሬት ይዞታ መብትን በተመለከተ ክርክር ሲነሳ አቤቱታ ለቀበሌው አስተዳደር ይቀርባል። አስተዳ□ሩ ጉዳዮ በሚመለከታቸው ተከራካሪዎች ፈቃደኝነት በተመረጡ የአካባቢው ሽማግሌዎች አማካይነት ታይቶ በእርቅና በትርትር እንዲፈታ ያደርጋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በሽማግሌዎች እርቅና ድርድር ያልተስማማ ወገን ለወረዳ መደበኛ ፍ/ቤት አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው።
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተሰጠው ውሣኔ ያልተስማማ ለከፍተኛ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 በተሰጠው ውሣኔ ቅሬታ ያለው ወገን ለጠቅላይ ፍ/ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል። በዚህ ደረጃ በአ/ቤት የሚሰጥ ውሣኔም የመጨረሻ ይሆናል።
5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት በተሰጠ ውሣኔ መሠረ□ዊ □ሕፅ ስህተት ይኖራለ ተብሎ ከታሰበ በሰበር ችሎታ ሊታይ ይችላል።

አንቀጽ 16. <u>የሌሎች ህጋዊ አካላት በገጠር መሬት የመጠቀም መብት</u>

1. ለከፊል አርብቶ አደሮች ቅድሚያ በመስጠት፣
   ሀ. በእንስሳት እርባታ፤ በእርሻ ስራና በተፈጥሮ ሃብት ልማት ለሚሰማሩ ባለሀብቶች በፌዴራልና በክልል ደረጃ በወጡት የኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችና ሕጎች መሠረት በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል።
   ለ. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተቋማት ከክልሉ የልማት ዓላማዎች ጋር እየታየ በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ይኖራቸዋል።
2. የሌሎች ባለይዞታዎች በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የጊዜ ገደብ ይኖረዋል። □ር□ሩ በደንብ ይወሰናል።

3. የገጠር መሬትን በሊዝ የተከራየ ባለሀብት የመጠቀም መብቱን እንደዋስትና ለማስያዝ ይችላል፡፡
4. ማንኛ□ም በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የተሰጠው ሕጋዊ አካል በመሬቱ ላይ በጉልበቱና በገንዘቡ ያፈራውን ሀብት ለሌላ ሕጋዊ አካል የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የመስጠት፣ የማውረስና በዋስትና የማስያዝ መብት አለው፡፡
5. ማንኛውም ግለሰብ ወይም ድርጅት ያለይዞ□ ማረ□ቱ □ብተር □ቹ□ር መሬትን መጠቀም አይችልም፡፡

አንቀጽ 17. የሌሎች ህጋዊ አካላትን መሬት ስለመለካት፣ ስለመመዝገብና □ጁዞታ ማረጋገጫ ደብተር ስለመስጠት

1. በመንግሥትና መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ይዞታ ሥር ያሉ የገጠር መሬቶች እንደሁኔታው ባህላዊና ዘመናዊ የቅየሣ መሣሪያዎችን በመጠቀም በመቀየስ፤ የመሬት ስፋታቸውን በመለካት እንዲሁም የመሬት አጠቃቀማቸውንና የለምነት ደረጃቸውን በመለየት በ□□ረጸ□ በሚቋቋሙ የመረጃ ማዕከላት ይመዘገባሉ፡፡
2. መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች የግል ባለኃብቶችና ማህበራዊ ተቋማት የይዞታ ባለቤትነት ማረጋገጫ ደብተር ይሰጣቸዋል፡፡
3. የገጠር መሬት በማን ይዞታ ሥር እንደሚገኝ፤ ከማን መሬት ጋር እንደሚዋሰን፣ ደረጃው ምን ዓይነት እንደሆነ፤ ለምን አገልግሎት እንደሚውልና ባለይዞታው ምን መብትና ግዴታዎች እንዳሉበት የሚገልጽ መረጃ ተመዝግቦ አግባብ ባለው አካል እንዲያዝ ይደረ□ል፡፡
4. በሊዝ ወይም በኪራይ የተያዘ የገጠር መሬት አግባብ ባለው አካል መመዝገብ አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

□አል አራት

ማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ ግዴ□ እና በመሬት አጠቃቀም የተጣሉ ገደቦች

አንቀጽ 18. ማንኛውም የገጠር መሬት ተጠቃሚ ግዴ□

1. በገጠር መሬት የመጠቀም መብት ያለው ማንኛውም አካል እንደመሬቱ የጥቅም ዓይነት (ለግጦሽ፣ ለ□ርሻ □□ተ...) እየታየና ሌሎች ታሳቢዎችን ግምት ውስጥ በማስገባት በመሬቱ የመጠቀሚያ ግብር የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡ □ር□ሩ በደንብ ጽ□ሰናል፡፡
2. የገጠር መሬት ባለጽዞታው መሬቱን በአግባቡ የመጠቀምና የመንከባከብ ግዴታ አለበት፡፡ በመሬቱ ላይ ጉዳት ካደረሰ የመጠቀም መብቱን ሊያጣ ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
3. የመስኖ ቦዮችና ሌሎች የመሠረተ ልማት አውታሮች በሚዘረቱበት ወቅት በባለጽዞታው መሬት ላይ የሚያልፍ ከሆነ ባለይዞታው ይህንኑ የመፍቀድ ግዴታ አለበት፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
4. ባለጽዞታው አግባብ ባለው አካል □ቹ□ር መሬቱ እንዲለካ □ጽም □ቅ□ዛ ሥራ እንዲካሄድ ሲጠየቅ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
5. ማንኛ□ም ባለጽዞታ የመጠቀም መብቱን በፈቃዱ ሲተው አግባብ ላለው አካል □ምላ□ቅ ፅጻታ አለበት፡፡ የይዞታ ማረጋገጫ ደብተሩንም ለሚመለከተው አካል መመለስ አለበት፡፡ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
6. ግለሰቦች፤ ባለሀብቶች፣መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በመሬት ለመጠቀም የሚያቀርቡት የልማት ዕቅድ የአካባቢ ደህንነት የሚያናጋ መሆን የለበትም፡፡ እነዚህ አካላት የአካባቢውን ደህንነት ጉድተው ከተገኙ አግባብ ባለው ሕግ ተቀጥተው አካባቢውን ወደ ነበረበት ሁኔ□ □መመለስ ፅጻ□ም አለባቸው፡፡ ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
7. ማንኛ□ም ባለሃብት የተከራየውን መሬትና በመሬት ላይ የሚገኘውን የተፈጥሮ ሀብትን የመንከባከብ ግዴታ አለበት፣ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
8. ማንኛውም ግለሰብ ሆነ ድርጅት በተከራየው መሬት ላይ አግባብ ያለው የመሬት አያያዝ ሥራዎችን በኪራይ ዘመኑ ተግባራዊ የማድረግ ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፣ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

9. ይዞታውን በተሻለ ደረጃ ለያዘና ለተጠቀመ አርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር እንዲሁም ባለሃብት የክልሉ መንግስት በጥናት ላይ ተመርኩዞ ማበረታቻ ይሰጣል፡፡ አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል፡፡

አንቀጽ 19. በገጠር መሬት የመጠቀም መብት የሚታጣባቸው ሁኔታዎች

1. ማንኛውም የመሬት ተጠቃሚ ሕጋዊ አካል የመጠቀም መብቱን የሚያጣው መሬቱ ለበለጠ የሕዝብ ጥቅም ሲፈለግና በሕብረተሰቡ ተሣትፎ ሲወሰን ብቻ ነው፡፡ □ር□ሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
2. መሬቱን በአግባቡ ተንከባክቦ ካለመጠቀም የተነሣ በመሬቱ ላይ ጉዳት ሲደርስና በቅጣት ብቻ ሊ□ለአ □ማጁቻል ሆኖ ሲገኝ የመሬቱ ተጠቃሚ የመጠቀም መብቱን ጸ□ል፣□ር□ሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
3. ማንኛ□ም የመሬት ተጠቃሚ ያለበቂ ምክንያት አግባብ ባለው አካል ከሚሰጠው □ዚ□ ቱ□ብ በላጁ መሬቱን ጦም ካሳደረ ወይም ካላለማ የመጠቀም መብቱን ጸ□ል፣□ር□ሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

አንቀጽ 20. □ቹ□ር መሬት አጠቃቀም ዕቅድ ስለማውጣትና ስለተዳፋት፣ ቦረቦርና ረግረጋማ መሬቶች አጠቃቀም

1. የአፈር ዓይነትን፣ የመሬት አቀማመጥን፣ የተዳፋትነት መጠንን፣ የአየር ፀባይን፣ የዕፅዋት ሽፋንንና ሶሺዮ-ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን ባካተተ መልኩ ተፋሰስን መሠረት ያደረገ የመሬት አጠቃቀም መሪ ዕቅድ አግባብ ባለው አካል ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ይሆናል፡፡
2. በላጁኛ□ና በታችኛ□ □ኮኛስስ □አል ባለ ተ□ቃሚ ሕብረተሰብ መካከል ፍትሃዊ የሆነ የውሃ አጠቃቀም ሥርዓት እንዲኖር ይደረጋል፡፡
3. የአፈርና ውሃ ጥበቃ ሥራዎች በተከናወነባቸውና በሚከናወንባቸው እንዲሁም ቋሚ ተክሎች በለሙበትና በሚለሙበት በማንኛውም ዓይነት የገጠር መሬት ላጁ ልቅ □እንሰሳት ግጦሽ የተከለከለ ነው፡፡ ስለሆነም አጭዶ የመመገብ ሥርዓት በአካባቢው ተግባራዊ ይደረጋል፡፡
4. የመሬት ተዳፋትነታቸው ከ 30 ፐርሰንት በታች የሆኑ የገጠር መሬቶች አያያዝ የአፈር ክለትን የሚቀንስና ውሃ የመሰብሰብን ስልት የተከተለ መሆን አለበት፡፡ □ር□ሩ በደንብ ይወሰናል፡፡

5. የመሬት ተዳፋትነታቸው ከ31 - 60 ፐርሰንት የሆኑ የገጠር መሬቶችን ለፐመታዊ ሰብሎች ልማት ለማዋል የሚቻለው ጠረንጴ□ማ እርከን በመስራት ብቻ ነው።
6. ተዳፋትነታቸው ከ60 ፐርሰንት በላይ የሆኑ የገጠር መሬቶች ለእርሻና ለልቅ ፅፌሽ እንዳይውሉ ሆኖ ለዛፍ፣ ለቋሚ ተክሎችና ለእንሰሳት መኖ ልማት እንዲውሉ ይደረጋል።
7. በማንኛውም ተዳፋት የሚገኝና በጣም የተጐዳ የገጠር መሬት ለተወሰነ ጊዜ ከሰውና ከእንሰሳት ንክኪ ተጠብቆ እንዲያገግምና ማገገሙ በወረዳው አግባብ ባለው አካል ሲረ□ጣ ዓቅም ላጁ እንዲውል ይደረጋል።
8. ቦረቦር የሆኑ የገጠር መሬቶች በግልና በአጐራባች ባለይዞታዎች፣ እንደአስፈላጊነቱም በአካባቢው ሕብረተሰብ ሥነ-ሕጁ□ታዊ እና ፊዚካላዊ ሥራዎችን በመጠቀም እንዲያገግሙና ጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረግ አለባቸው።
9. በኮረብታ አካባቢዎች ያሉ ቦረቦር የሆኑ የገጠር መሬቶች በወል እንዲሁም እንደየሁኔታው በግል ተይዘው እንዲያገግሙና እንዲለሙ ይደረጋል።
10. ረፅረ□ማ □ሆኑ የገጠር መሬቶች ያላቸው ብዝሀ-ሕይወት እንዲጠበቁና ተስማሚ በሆነ የመሬት አጠቃቀም ስልት ጥቅም እንዲሰጡ ጁ□ረ□ል። □ር□ሩ በደንብ ይወሰናል።
11. በ□ል ጁዞታነት የሚታወቁ የተጐዱ መሬቶች በህብረተሰቡ ተሳትፎ በአግባቡ እንዲያገግሙ ይደረጋል፣ የሚለሙበትም ሁኔታ ይቀየሳል። አፈጻጸሙ በደንብ ይወሰናል።
12. ለደን፣ ለዱር እንሰሳት፣ ለአፈር ጥበቃና ልማት፣ ለማዕድን ልማትና ለታሪካዊ ጠቀሜታ የተከለሉ መሬቶች ከአጠቃላይ ሥነ-ምህዳር ጁዞታቸው ጋር በዘላቂነት እንዲጠበቁ ይደረጋል። እነዚህ የተጠበቁና የተከለሉ አካባቢዎች አግባብ ባለው አካል በሚወጣ ሕግ ይተዳደራሉ።
13. በመንግሥት ይዞታ ሥር ባለ የደን መሬት ውስጥ የሚገኙ እንጨት ያልሆኑ የደን ሀብቶችን /ከርቤ፣እጣን፣ሙጫ..... ወዘተ/ የአካባቢው ሕብረተሰብ የመጠቀም መብት ይኖረዋል። ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡

ክፍል አምስት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

አንቀጽ 21. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚቋቋመው አካል ኃላፊነት፣

1. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ሥርዓትን የሚያስፈጽሙ ተቋማት በተ□ረት እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ □ማትረፅ ኃላፊነት አለበት፡፡
2. አግባብ ያላቸውን አካላት በማስተባበርና አስፈላጊውን የሙያ ድጋፍ በመስጠት ይህን አዋጅ የማስፈጸም ኃላፊነት አለበት፡፡
3. በወረዳ ደረጃ የተሰባሰቡና በየጊዜው በክትትልና በግምገማ የሚገኙ መረጃዎችን መሠረት በማድረግ አዳዲስ ሀሣቦች እንዲነደፉና በ□ዚ□□ እንዲሻሻል ያደርጋል፡፡
4. በፌዴራልና በክልል እንዲሁም በወረዳዎች መካከል የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም መረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዲዘረጋ ያደርጋል፡፡
5. በቀበሌ ደረጃ የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ የማዋቅር ኃላፊነት አለበት፣ዝርዝሩ በደንብ ይወሰናል፡፡
6. የተሻለ የገጠር መሬት አጠቃቀም ሥርዓት ለማስፈን የሚያስችል በፍላጎት ላይ የተመሰረተ የተረጋጋ ኑሮ መምራት፣ መን□ር ምስረታና ማህበራዊ አገልግሎቶች የሚስፋፉበትን ስልት እንዲነደፉ ያደርጋል፡፡

አንቀጽ 22. የገጠር መሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ ኃላፊነት

1. በቀበሌ ደረጃ የሚቋቋመው የመሬት አስተዳደርና አጠቃቀም ኮሚቴ አዋጁን ለማስፈጸም የሚቋቋመው አካል በቀበሌው ውስጥ ከሚመድበው ወይም ከሚሰይመው ጋር በመተባበር ይህን አዋጅ በማስፈጸም ረገድ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል፡-

ሀ. በቀበሌው ውስጥ የሚገኘውን መሬት ያስተዳድራል፤ የመሬት አጠቃቀም በወረዳ ደረጃ ከሚቋቋመው አግባብ ያለው አካል ትብብር በህዝብ ተሳትፎ እንዲወሰን ያደርጋል፡፡

ለ. የሚቀርብለትን የመሬት ጥያቄ ተቀብሎ በህዝብ ተሳትፎ እየታገዘ ቅድመ ተከተል በማስያዝ የመሬት ጉዳዮችን ያስፈጽማል፡፡

ሐ. ከክልሉ አግባብ ያለው አካል በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የቀበሌውን የመሬት ባለይዞታዎችና የይዞታ ማረጋገጫ ደብተር የተሰጣቸውን ሌሎች ባለይዞታዎችን መዝግቦ ይይዛል፡፡

አንቀጽ 23. □መተባበር ፅጻ □

ማንኛውም ሰው ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አግባብነት ካላቸው አካላትት ጋር የመተባበር ፅጻ ታ አለበት፡፡

አንቀጽ 24. ስለቅጣት

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ ወይም አዋጁን ለማስፈጸም የወጡ ደንቦችንና መመሪያዎች ጥሶ ሲገኝ አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

አንቀጽ 25. ስለተሻሩና ተፈጻሚ ስለማይሆኑ ሕጐች፣

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ የተደረገጉትን ጉዳዮች በተመለከተ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

አንቀጽ 26. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን ፣

1. የክልሉ መስተዳድር ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚረዳ ደንብ ያወጣል፡፡
2. ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚቋቋመው አካል በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትሎ በሚወጣው ደንብ መሠረት የአፈጻጸም መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

አንቀጽ 27. የመሸጋገሪያ ድንጋጌ

1. በክርክር ላይ ያሉ (ውሣኔ ያላገኙ) ጉዳዮች በሙሉ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ተ□ነሚ ይሆናሉ፡፡
2. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ከገጠር መሬት ይዞታና ከመጠቀም መብት ጋር ተያይዘው በሌሎች ህጎች የተቋቋሙ መብቶችና ግዴታዎች ይህንን አዋጅ እስካልተቃረኑ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል፡፡

አንቀጽ 28. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከዛሬ ሀምሌ 9 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ሰመራ ሀምሌ 9 ቀን 2001 ፒ.ም

አቶ ኢስማዔል አሊ ሴሮ

□አፋር ብሔራዊ □ልላዊ መንግሥት ርዕሰ መስተዳድር